# ስለ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ሁኔታ ግንዛቤ፣ አስተያየትና አጭር ምክረ ሀሳብ

ከፕሮፌሰር ጌታቸው መታፈሪያ

የካቲት 15 ቀን 2015/ February 22, 2023

ይህችን ግልፅ ደብዳቤ ለመጻፍ ያስገደደኝ እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የአገራችን ሁኔታ እጅጉን ስለአሳሰበኝና ብሎም ዘላቂ መፍትሔውም በቅርብ ስለአልታየኝ ነው። የአገር ህልውና፣ የስብዓዊ መብቶች፣ መልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ የመሳሰሉት መሠረታዊ ጉዳዮች በጥንቃቄና በአርቆ አስተዋይነት ካልተያዙ ተሰባሪ ሸክላዎች ናቸው። አንዴ ከተሠበሩም ጠግኖ ወደ ቀድሞው መመለስ ያዳግታል። በቅርቡም ጠንካራ የነበሩ መንግሥታትና አገራት ምን እንደሆኑ እናውቃለን።

የአገራችን ሁኔታም እንዲሁ መታየት አለበት። እስከአሁንም በከንቱ የንጹሐን ደም ፈሶብናል፣ ልብ ተሰብሯል፣ ኑሮም ተናግቷል። ይህ ወደ ባሰና ወደ አስከፊ ሁኔታ እንዳይሸጋገር፣ ለመሪዎቻችንም አስተዋይ ልቦና እንዲሰጣቸውና ያንዣበበው ጽልመተ ሞት ተገፎ በመቻቻል ዘለቄታዊ ሰላም እንዲወርድ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከፖለቲካ መሪዎችም የሚጠበቁ ተግባራት አሉ። ለእነኝሁ መሪዎችም ሰሚ ጆሮ፣ አስተዋይ ልቦና እንዲሰጣቸውና ሚዛናዊ የሆነ አመለካከት እንዲኖራቸው ይመረጣል።

አሁን በተለይም ለገዢው ፓርቲና ለጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ አህመድ ከሌሎች አገር ተቆርቋሪ ግለሰቦች ጎን ተሰልፌ በዚህ በቀውጢ ቀን ድምፄን አሰማለሁ።

## ግንዛቤ

ክቡር ጠ/ሚኒስቴር ወደዚህ ሥልጣን ሲመጡ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሚነግሯቸው ተስፋ ሰጪ ቃላትና ከእርሶ በፊት ከነበረው አመራር በተለዬ መልኩ ትህትናዎንና የኢትዮጵያ ትንሣኤ መቅረቡን በተለያዩ

ህብረቀለማት በተጌጡ ቃላት በማሰማቶ ቀልቡን ስበውት ነበር። እኔና አብዛኛው በውጪ ሀገራት የምንገኘው ኢትዮጵያውያን ደግፈኖት ዕድሉንም ሰጥተኖት ነበር። ራዕይ ኢትዮጵያ ወይም ቪዥን ኢትዮጵያ ባዘጋጀው የዋሽንግተን ከተማ ጉባኤ ላይም በወቅቱ ካሳዩት አወንታዊ ሁኔታ ተነስቼ ከአንዳንድ የፖለቲካ ፈላስፎችና ታዋቂ መሪዎች ጋር አንጻጽሬ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርቤ ነበር። አንዳንዶቹ መሪዎችም በቃላት የሚናገሩትን በተግባር ማሳየት ካልቻሉና በመጨረሻም የህዝቡ ብሶት መልስ ካላገኘ መጨረሻቸው ላያምር ይችላል ብዬ ጠቁሜ ነበር።

በታሪክም ሆነ በዘመናችን የዚህ ምሳሌ አያሌዎች ናቸው። ከአሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከፈረንሳዊቷ ልዕልት ማሪ አንቶኔት፣ከዚያው አገር መሪ የነበረው ናፖሊዮን ቦኖፓርት፣ በዘመናችንም እንደ አሜሪካዊው ሪቻርድ ኒክሰን፣ የፊሊፒንስ ፌርዲናንድ ማርቆስና በክፍለ አህጉራችንም እንደ ሟመር ጋዳፊ ይገኙበታል። ሁላቸውም እንግሊዛዊው ጆን ዳልበርግ አርቶን እንደጻፈው “ሥልጣን ያባልጋል፣ ፍጹም ሥልጣን ፍጹም ያባልጋል” ለሚለው አባባል ሰለባ ሆኑ።

ክቡር ጠ/ሚኒስቴርም የዚህ አባባልና ሁኔታ ሰለባ እንዳይሆኑ ቆም ብለው ያስተውሉ። ታሪክም ጥሩ አስተማሪ ነውና የጥንት የኢትዮጵያ መሪዎች እንኳን “ሰው ምንብሎ ያጉረመርብብኛ?፣ አዝማሪና እረኛስ ምን አሉ?” እያሉ የህዝቡን ቅሬታ ለማወቅ ይጥሩ ነበር ይባላል። ወጣት እረኛም የአዋቂዎቹን ጉምጉምታና ብሶት ሰምቶ በእንጉርጉሮው ሽለቆውን ያስተጋባል ይባላል። ደብተራውም በሰምና ወርቅ ቅኔ መሪው ፊት ቆሞ ቅኔውን ይዘርፍ ነበር። ውስጠ ወይራው የገባውም፣ ያልገባውም ያጨበጭባል። ለዚህም ነበር መሪዎች ህዝቡ ከነሱ ጋር መሆኑና መደሰቱን ወይም መቀየሙን ለማወቅ እረኛ፣ አዝማሪ በግጥሙ፣ አልቃሽ በሙሾ ምን አሉ? የሚሉት። አሁን ግን በአጭር የአስተዳደር ዘመንዎ አመራሮ አጠያያቂ ሆኗል። ህዝቡም እነሆ በገሐድ ወጥቶ ህገ መንግሥታዊ መብቱን ለማስጠበቅ መንግሥቶን እንደ ተፈታተነው ታይቷል።

አንድ መሪ አማካሪዎቹም ሆኑ የካቢኔ ሚኒስትሮች አብዛኛዎቹ አንድ ወጥ አመለካከት ያላቸውና የአገሪቷን ስብጥር ህብረ ብሔራዊነትን የማያመላከቱ ከሆኑና ልዩ ልዩ አስተያይቶችን ካላስተናገዱ የሚያፈልቁት ፖሊሲና መንግሥታዊ አቋም ወደ አንድ ጎን ያጋደለ ይሆናል። ምልክቶቹም እነሆ እየታዩና ልዩ ልዩ እሮሮዎች እየተሰሙና ደም እየፈሰሰ ነው። እሮሮዎችም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየመረሩና እየታዩ ነው። ብዙ ጊዜ የሥርዓት/

የአስተዳደር ነቀፋውን መሰሪ ሰዎች ወደ ብሔር ጥላቻ ስለሚወስዱት ሁሉም ሰው ከዚያ አደገኛ ስሌት መገታትና ወጥመድ ውስጥ እንዳይገባ መቆጠብ አለበት። ለዚህም ነው ታሪካችንን መማርና የህዝቡን ስብጥርነት ማወቅ አስፈላጊነቱ። በዚያ ላይም መሪን መፍራትና ላለማስቀየም ተብሎ ያለመናገርና እራስን መግታት አለ። በራሳቸው የማይተማመኑ መሪዎች ቂመኞች ናቸውና። ይህም እንዳይሆን ነበር ፕሬዜዳንት ኬኔዲ ቤ ኦፍ ፒግስ (The Bay of Pigs) በሚባለው ኪዩባን ለመውረር በ **1961** በታቀደው አስጨናቂ የካቤኔያቸው ስብሰባ ላይ ተወያይታችሁ የምወስደውን እርምጃ ንገሩኝ ብለው ፕሬዚዳንቱ ከስብሰባው የወጡት። ከሁሉም በላይ የፕሬዚደንቱ ወንድም የፍትህ ሚኒስቴር የነበረው ሮበርት ኬኔዲ ታላቅ ወንድሙ ሦስተኛውን የዓለም ጦርነት እንዳያስነሳ በካቢኔ ስብሰባው ላይ የተጨነቀ፣ የተጠበበና ከሌሎችም የተለየ ሥጋት ነበረው ይባላል። ወቅቱም ቀዝቃዛው ጦርነት የጋለበት ነበር።

## *<u>ወቅታዊ ሁኔታ</u>*

በአገራችን አሁን በቤተ ክህነት ውስጥ በተፈጠረው አለመግባባትና የመንግሥት አቋም ጥርጣሬ ውስጥ ስለገባ አገራችን ወሳኝ በሆነ መስቀለኛ መንገድ ላይ ቆማለች። የሙስሊሙ ህብረተሰባችንም የታመቀ ቅሬታው ገንፍሎ አሁን ወጥቷል። ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ህዝብ ጭንቀት፣ ፍርሐትና ስጋት ጥግ የደረሰው። ሁኔታዎችም ዱብ ዕዳ ሳይሆን ቀደም ብሎ በህወሃት አገዛዝና ከበፊቱም ጀምሮ ተጠንቶና ተቀነባብሮ አሁን ሥራ ላይ እየዋለ ነው። ችግሮቹን የሚያመላክቱና ጠቋሚ የሆኑትን ለመገንዘብ የህብረተ ሰብ አጥኚዎች (Social Scientists ወይም Behavioralist) መሆንን አይጠይቅም። በገሐድ ሰዎች ከኖሩበትና ከተወለዱበት ቀዬ በጎሠኞችና በሃይማኖት ተኮር አነጣጥሮ ማፈናቀልና መግደል የጤንነት ምልክት ወይም የመልካም አስተዳደር ውጤት አይደለም። አስተዳደሩም ውስጥ አያሌ ችግሮች እየተከሰቱ ነው። የገዛ ወገኑን አሰቃይቶና አፈናቅሎ ለአፍሪካ አንድነትና ለፓን አፍሪካ ወድማማችነትና እህትማማችነት እንቆማለን ማለት "ከአንድ እራስ መንታ ምላስ" በላይ የፓን አፍሪካ መሪዎችንና አባቶች እንደ ክዋሜ ኑክሩማና መዋሊሙ(መምህር) ኔሬሬና ሌሎችም ላይ ማፌዝ ሆኖ ይቆጣራል። ነሬሬ ህዝባቸውን በአንድ አገራዊ ስዋሒሊ ቋንቋና አገራዊ ሥርዓተ ትምህርት አስተሳሰሩት። ታንጋኒካና ዛንዚባርን በማዋሃድ የአሁኗ ታንዛኒያ ፈጠሩ። ይህ ነው አገር ግንባታ የሚባለው። እኛ ግን አገር

መገንባት ሳይሆን አንድ እርምጃ ወደፊት፣ ሁለት እርምጃ ወደ ኃላ እያልን እንዳከራለን። ይህም ሆኖ ግን አፍ መፍቻ ቋንቋ ሰብአዊ መብት መሆኑ አይዘነጋም። የአፍሪካ ህብረትም አፍሪካውያኖች በአህጉሩ ውስጥ በነፃነት እንዲዘዋወሩ ዲፕሎማሲያዊ መግባባት በሚደርሱበት (Protocol) ወቅት እኛ አገር ግን እውነታው ሌላ ነው። ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ ችግር ሆኗል። ይህም የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው።

ቁም ነገሩ ማንም ባለሥልጣን እንደሥራው ዘርፍና ኃላፊነት ከተጠያቂነት ማምለጥ የለበትም። ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ሁኔታዎች ሳይታሰቡ፣ ሳይጠኑ ዱብ ዕዳ አይሆኑም። ለተከሠቱት ሁሉ ተጠያቂነትና ኃላፊነት መኖር አለበት፣ አላውቅም ለማለትም አይቻልም። በህዝብ ደም፣ እንባና ሥቃይ መቀለድ መቆም አለበት። ያለበለዚያ ህግ አለ ለማለት አይቻልም። በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአሁኑ አልጀሪያ፣ ሰሜን አፍሪካ የነበረው ቅዱስ አጉስቲን፣ ፈላስፋና የሥነ መለኮት መምህር የፍትህ አስፈላጊነትን ሲያስተምር "ፍትህ በሌለበት አገር ህገ ወጦች ይሰፍኑበታል፤ ሁሉም በሁሉም ላይ ይዘምታል" በማለት አስተምሮ ነበር። በዚህም በአሥራ አንደኛው ሰዓት ላይ መጮህ ያለብን ይህ በሀገራችን እንዳይከሰትና አሁንም እንዳይባባስ የተነሳውን ቋያ ሰደድ እሳት ለማጥፋት መረባረብ ነው። እሳቱ የሁሉንም ቤት ሊያጋየው ይችላል።

የሰው ልጅ እንደ አጉስቲን አስተምህሮ፣ ለህገ እግዚአብሔርና ለህገ መንግሥት መገዛት ተገቢ ነው። ነገር ግን  በሁለቱ ህግጋት መሐከል ቅራኔ ወይም አለመጣጣም ከተፈጠረ ቅድሚያ ለህገ እግዚአብሔር ይሰጣል። ምክንያቱም የህገ መንግሥት ምንጩ ህገ እግዚአብሔር ስለሆነ (God's Law) ነው ብሎ አስተምሯል። በየዘመኑ ህገ መንግሥታት፣ የፖለቲካ አመለካከት ወይም ፍልስፍና ርዕዮተ ዓለም ሲለዋወጡ ህገ እግዚአብሔር ግን ለወቅቱ የፖለቲካ ፍጆታ የሚውል አይደለም። ስለዚህም ይህ መለኮታዊና ግብረገባዊ ትምህርት በሥነ ልቦናችን የተፃፈው መከበር አለበት። በአብዛኛው አብረሃማዊ ሃይማኖቶች የሚባሉት (ክርስትና፣ እስልምናና ይሁዲ) ይህንን ያመላክታሉ።

በዚህ ክቡር ህግ የተንፀባረቁትን መንግሥታት ከጣሱት፣ ሚዛናውነት ከጎዶላቸው፣ ፍትህ ከተረገጠ ህዝቡ ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ተቃውሞውን መግለጽ አግባብነት አለው በማለት መነኩሴው ፈላስፋ አውግስቶስ አስተምሯል። በዚህ ላይ ተመርኩዘው በ17ኛውና በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት ብቅ ያሉት የእንግሊዝ

ፈላስፋዎች ቶማስ ሆብስና ዮሐንስ ሎክ፣ እንዲሁም የፈረንሳዩ ጄን ሩሶ በመንግሥትና በህዝብ መሐከል የሚገባ ውልና ኮንትራት (Social Contract) አለ ብለው የፖለቲካ ፍልስፍና አስተማሩ። ይህም ውል የህዝብንና የመንግሥትን መብት፣ ግዴታና ገደብ ያስቀምጣል። የእነኚህ ፈላስፍዎች አስተምሮ ልቅ ዴሞክራሲ ( liberal democracy) ፍልስፍና በሚከተሉ እንደ አሜሪካና ፈረንሳይ ባሉት ህገ መንግሥታት ውስጥ ተንፀባርቀዋል፣ ሥራም ላይ ውለዋል። የግለሰብ ነፃነት፤ የሃይማኖትና ፖለቲካ መለያየት፣ በነፃነት ከቦታ ቦታ መዘዋወር፤ የመንግሥት መዋቀር መከፋፈልና (Checks and Balances) ገደብ ማበጀት ሁሉ የነዚህ ፈላስፋዎች ውጤት ነው። ስለሆነም መንግሥት የስልጣን ወሰኑንና ገደቡን ጥሶ ፍርድ ካዛነፈ፣ ካጎደለ፣ ወይም የህዝብ ነፃነት ካላከበረና ገደቡን ከጣሰ ( Civil liberty) መንግሥት ላይ ሰላማዊ እንቢተኛነትን መከተልና ህዝባዊ ቅቡልነትና አመኔታ ባጣ መንግሥት ላይ ህዝባዊ ቁጣ መግለፁ አግባብነት አለው ብለው አስተምረዋል።

ይህም አስተምሮና ፍልስፍና በግብር የተተረጎመው በህንድ አገር በማኅተመ ጋንዲ ቀስቃሽነትና ትግል የእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ተደረመሰ። ይህንኑ ፈለግ በመከተል በአሜሪካ ማርቲን ሉተር ኪንግ የክርስትና ሃይማኖት ሰባኪ የጥቁር አሜሪካኖችም ህጋዊና ሰብዓዊ መብቶቻቸው (Civil Rights) በህገ መንግሥቱ የተጻፈው ተግባራዊ እንዲሆኑ ታግሎና አታግሏል። በሚያሳዝን ሁኔታም ሁለቱ ታጋዮች ብርሃናቸውን አፈንጥቀው፣ ትግላቸውም እንዲቀጣጠል አድርገው በተቀነባበረ ሁኔታ በዜጎቻቸው እጅ የሞት ጽዋ ተጎንጭተው ተሠውተዋል። ያቀጣጠሉትም ትግል አሁንም ጨቋኝ መንግሥታትንና ሥርዓቶችን የፍትህና የፖሊሲ ተቋማትን በዓለም ደረጃ እያታገል ነው። እንደ ጋንዲና ኪንግ በሳንሳልቫዶር የካቶሊክ ጳጳሱ ኦስካር ሮሜሮ (ኋላ ቅዱስ) የተባሉት በ 1980 አንባገነን መንግሥትን አጥብቀው የሚቃወሙና ለድሃ የቆሙ ሥርዓተ ቁርባን ምዕመናን በሚቀበሉበት ጀርባ (altar) በጥይት ተገደሉ።

በደቡብ አሜሪካም በዩኒቨርሲቲ ምሁራንና ደቀመዛሙርቶቻቸው የተጧጧፈው መለኮተ አርነት ( Liberation Theology) አብዛኞች ማርክሲስትና ካቶሊክ የሆኑ ታጋዮች አንባገነኖችን ታግለዋል፣ ተሠውተዋልም። በእሲያም ቢሆን ቡዲስት መነኮሳት ከአንባገነን መሪዎች ጋር በደቡብ ቪየትናም፣ በታይላንድና በበርማ ለወትሮው ሰላማዊ የሆኑ፣ ከተፈጥሮና ከራስ ጋር መታረቅና መዛመድን (በሜዲቴሽን) የሚያዋህዱ

ቢሆንም ባልተጠበቀ ሁኔታ አንባገነን መንግሥታትን ሲታገሉ ታይተዋል። ምሬታቸውን ለመግለፅም እራሳቸውን በእሳት እስከ ማጋየት ደርሰዋል።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጠ/ሚኒስቴሩ በመንግሥት ሴራ የተከፈለችውን ሐዋሪያዊት ሲኖዶስ ወደ አንድነት በማምጣታቸው ስታስታውሳቸው ትኖራለች ብዬ አስባለሁ። ነገር ግን የኋላ ኋላ ያከበረችና ያቀፈቻቸው የአገር መሪ በሃይማኖቷ ተከታዮችና በሌሎችም ላይ በሚደርሰው ግድያ፣ መፈናቀልና ሰቆቃ ዝምታን መምረጣቸው አጠያያቂ አድርጓቸዋል። ስለሆነም ደጋፊዎቻቸውም ተስፋ በመቁረጥ ሰውዬው ወዴት እያመሩ ነው የሚለውና ተስፋ የቆረጠባቸው መበራከቱ የአደባባይ ሚስጢር ሆኗል። በቅርቡ አንዱ እንዳጫወተኝ "ዓብይን ደግፌ አገሬ ሄጄ፣ ተቃዋሚ ሆኜ መጣሁ" ብሎኛል። አሁን ደግሞ ህገ ወጦችንና ቤተ ክርስቲያን ከፋፋዮችን ከለላ ሰጡ ተብሎ የኦርቶዶክስ ህዝበ ክርስቲያን ተናዷል። አሃቲ ቤተ ክርስቲያንና ሲኖዶስን በመደገፍና አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖቻቸው እንዳትሰበር ህገ ወጦችን በሰላማዊ መንገድ ለመግታት ዘብ የቆሙትን ህዝበ ክርስቲያን ምዕመናንን አባቶችና እናቶች አገልጋዮች ላይ መብታዊ ጥሰት ተፈጽሞባቸዋል። ጠ/ሚኒስትሩ አስታርቃለሁ ብለው ተገንጣዮቹን፣ ፓትሪያርኩንና የሲኖዶሱን አባላት ማገናኘታቸው ደስ የሚል ቢሆንም ምዕመናኑና ደጋፊዎች ጥርጣሪያቸውና ሥጋታቸው አልተወገደም። እርቅና ይቅርታው ምንም ያህል በሥራ እንደሚተረጎም ገና አልታወቀም። የዜጎች መፈናቀል ቀጥሏል። ይህ በዘመናችን መከሰቱ አሳፋሪ ነው። የጠ/ሚኒስትሩ አመራርና ፌደራሊዝም የመፈተኛቸው ጊዜ ነው። ሁኔታውም በየጊዜው ተለዋዋጭና አስጊ ሆኗል። ሰላም ወረደ ሲባል በነጋታው ደግሞ ተቀለበሰ ይባላል። ይህ ለተመልካችም ግራ የገባውና የልጅ ጨዋታ ሆኗል።

ከዚህ በላይ በተገለጹት የመንደርደሪያና ለግንዛቤም ትምህርታዊ መረጃዎች ካቀረብኩ በኋላ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን፣ በተገንጣይ አባቶችና በመንግሥት መሐከል የተፈጠረውን አሳሳቢና ወስብስብ ሁኔታ ምዕመናን በእምነታቸው ጸንተው መሥዋዕትና አካለ ስንኩል ለሆኑት፣ ሰብዓዊ መብቶቻቸው ለተገፈፈው፤ ጸያፍ ድርጊት ለተፈጸመባቸው፣ እንግልት ለደረሰባቸው፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ልባቸውና ስነልቦናቸው ለተሠበረው መጽናናትንና መበረታታትን እየተመኘሁ እንባችሁ በከንቱ እንደማይቀር እምነቴ ነው።

## ከዚህ ቀጥዬ አጭር መልዕክቴንና መፍትሔ ሃሳቦች የመሰሉኝን ልስንዝር።

በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ስለ አሳያችሁት የሰከነ፣ ግብረገባዊና አስተማሪ በሆነ አቋማችሁና አመራራችሁ በጣም ኮርቼባችኋለሁ፣ ኮርተንባችኋል። ሃይማኖቷ ጥንታዊት ፣ ጥልቀት ያላትና ምስጢራዊት እንደሆነች ለዘመናት የቆየ ቀኖናና፣ ሥነ ሥርዓትና ህግጋት እንዳላት በገሐድ አስመስክራችኋል።

ባዕዳን፣ ዘረኛና ከእኛ በላይ አዋቂ የለም ለሚሉና ልቦና ያላቸው ሁሉ ታሪክ እንዲያውቁ አድርጋችኋል ብዬ አምናለሁ። ዛሬ የቆምነው በትላንት ታርክ ላይ ነው። መንግሥትንና በተለይም የውጪ ታዛቢዎች አገር ብትወረር እንደ አድዋው ጦርነት ይኸው እምቅ ኃይል ከሌሎች እምነት ተከታዮች ጋር ፣ ቋንቋና የዘመኑ ከፋፋይ ክልል ሳይገድበው እንደሚነሳ አስመስክራችኋል። ሁኔታው በፖለቲካ ሳይንስ ለስላሳና ጠንካራ ኃይል (Soft/hard Power) ተብሎ ለሚጠናውም አስተዋጸኦ አድርጓል። የዘመኑም ትውልድ ትምህርት አግኝቶበታል። ሆኖም ግን አገሪቷና ቤተ ክርስቲያኒቷ ከስጋት ተላቀዋል ማለት አይደለም። ብዙ የቤት ሥራ ይቀረናል። ለዘመናት የተቀበረው መርዝ ቀላል አይደለም። ይኸውም በህገ መንግሥት ደረጃ ከፋፋይ አንቀጾችን በማስገባት ፈንጂ ሁኔታዎችን በማዘል ኢትዮጵያ ቀዳሚ አገር ሆናለች። ስለዚህም አገራዊ መፍትሔ ለመፈለግ መነሻው ከህገ መንግሥቱ መጀመር አለበት። ያለበለዚያ ጊዜ ማባከን ነው።

ሁለተኛ፣ ይህ የአሁኑ ክስተት መንግሥት እወክለዋለሁ ለሚለው ህዝብ ባዕድ መሆኑን ያገናዝባል ብዬ አምናለሁ። መንግሥት ሆይ ፣ እራስህን ገምግም። "ሰው ለራሱ ባዕድ ነው" እንዲሉ ገለልተኞች እንዲያጠኑህም አድርግ። መንግሥት የህዝብን አመኔታ ካጣ እንደድሮው ተመልሼ እሆናለሁ ማለት ዘበት ነው። የተነቃነቀ ጥርስ አሽቼ ወደ ጥንቱ እመልሳለሁ እንደማለት ነው። የህዝቡን አቅም ለመገምገም ያዝ ለቀቅ ያለ እርምጃ መውሰድ አያዋጣም። መዘዙም ደግ አይሆንም።

ሮዶልፍ ግራዚያኒ በዚህ በወርሃ የካቲት አገሪቷን የአዲስ አበባን ወጣቶችና በተለይም ጥቂት የነበሩትን የተማረውን ኃይል የጨፈጨፈበት ወቅት ነበር። ገዳማትና ቤተ ክርስቲያናት አቃጥሏል፣ መነኮሳትንም

ጨፍጭፏል። አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል ዘጎሬ (በሀገረስብከታቸው መታሰቢያ ያልቆመላቸው) በጥይት ተደብድበዋል። ያ ታሪክ እንዳይደገም መታሰብ አለበት። በአባቶች መካከል እርቅ ወረደ ሲባል እውን እንዲሆን እንፈልጋለን። እንዲሁም ታች ወርዶ በሥራ ላይ መዋሉን ስናይ እርግጥ እርቅ ወረድ ይባላል። የኢትዮጵያ ህዝበ ሙስሊም ጥያቄ መፈታትና መንግሥትም በሃይማኖት ጣልቃ መግባቱን ማቆም አለበት። ስለዚህም "ሁሉም በሁሉም ላይ ይዘምታል" ያለው ቅዱስ አጉስቲን ካመከን ደስታው የሁላችን ነው።

በመጨረሻም ሁላችንም ለአሁኑ ችግር መንስኤ የሆኑትን መፈተሽና በአግባቡ መፍትሄ መሻት የግድ ይላል። በተለይ ቤተ ክርስቲያን እንደታላቅ ተቋም የምዕመናንን ብሶት ታድምጥ። አስተዳደሯንም ትመርምርና ከሙስና የፀዳች ትሁን። አንዳንድ አባቶች ላይ የሚሰማውን ቅሬታ፤ በውጪው አገር  በፍቅረ ንዋይ  ምክንያት ምዕመናን የሚከፋፍሉ፤ ይባስ ብለው ቤተ ክርስቲያን ሰብረው "ማርያም ከፈተችው" እያሉ የምዕመናንን ተስፋ አፈር የሚያለብሱ ሠልፍ አድማቂ ጉደኞችን ሁሉ አጥብቃ ትገስፅ። መንግሥትም በውስጡ ላሉት ችግሮችና መከፋፈል የአገሪቱን ህልውና ባስጠበቀ መልኩ መፍትሔ ይፈልግ። ቀደም ብሎ እንደተነገረው ማንም ግን ከተጠያቂነት ማምለጥ አይችልም። ከሙስናና በሥልጣን ከመባለግ መቆምና ህዝብን ማገልገል የመንግሥት ቋሚ መመሪያና ትግባራዊ መሆን አለበት። ቆም ብላችሁ ጆሯችሁን ለሕዝቡ ስጡት፤ ምክርና ግሳፄም አስተናግዱ። ህዝቡን የፖለቲካ ኤኮኖሚ ርዕዮተ ዓለምና የአዲስ ፍልስፍና መፈተሻ ቤተ ሙከራ አታድርጉት። አስተዳድሩን እንጂ አትግዙን።

ለማጠቃለል ይህ ወቅት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ለወደፊቱ የሚጠቅም ትልቅ የትምህርትና የዕውቀት ማዳበሪያ ጊዜ ነው ብዬ አምናለሁ። አገራችን ጠንክራ እንደምትወጣም አልጠራጠርም።

# ሰላም ለኢትዮጵያ